ሰበር ዜና

ዛሬ ጠዋት 4 ሰዓት ላይ የኢሳያስ መንግስት አየር ሃይል MIG 29 የጦር አውሮፕላን አብራሪ የሆኑት መቶአለቃ መብርሃቱ ተስፋማርያምና አፈወርቅ ጸሃዬ የተባሉ ሁለት ካፕቴኖች የክንፍ ቁጥሩ 102 የሆነውን ZLIN 143 አውሮፕላን ይዘው መቀሌ በማረፍ እጃቸውን ለኢትዮጵያ መንግስት መስጠታቸው ታውቋል።

ዛሬ ከጠዋቱ 3 ሰአት ከአስመራ የተነሳውና ስሪቱ የቼክ ሪፐብሊክ የሆነው ZLIN 143 አውሮፕላን ዋናው ተግባሩ የቅኝት ስራና የመለማመጃ እንደሆነ ታውቋል።

እንደ የኢትዮጵያ አየር ሃይል ምንጮች ከሆነ አውሮፕላኑ የኢትዮጵያ የአየር ክልልን አልፎ ከመግባቱ በፊት አብራሪዎቹ በአውሮፕላኑ ውስጥ ምንም ነገር አለመያዛቸውንና አደጋ የማድረስ ሃሳብ እንደሌላቸው አስታውቀው እጃቸውን ለመስጠት መምጣታቸውን በመግለጽ እርምጃ እንዳይወሰድባቸው ጠይቀው መቀሌ ለማረፍ ማስፈቀዳቸው ተገልጿል።

የኢትዮጵያ አየር ሃይል ይበልጥ እርግጠኛ ለመሆን እጃቸውን የሰጡት አብራሪዎች በእርግጥ አደጋ እንደማያደርሱና ምናልባትም ሌሎች አደጋ ለማድረስ ተከትለዋቸው የሚመጡ አውሮፕላኖች እንዳይኖሩ በሚል SU27 የጦር ጀቶች እንዲነሱ በማድረግ አውሮፕላኑ የኢትዮጵያ አየር ክልል ሲደርስ አጅበው መቀሌ እንዲያርፍ እንዳደረጉት ከኢትዮጵያ አየር ሃይል ከተገኘው መግለጫ ለማወቅ ተችሏል።

Ethiopiafirst.com facebook